# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## በልደት ሰሞን በሚውለው ሰንበት የሚፈጸመው ሥርዓተ አምልኮ

ዘመነ ልደት የሚባለው ከታኅሣሥ ፳፱ ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ ያለው ጊዜ ነው። በዚህ ሳምንት ውስጥ የሚዘመረው መዝሙር ልደትን ርደትን የሚያነሳ ይሆናል።

### የዕለቱ ምስባክ

ወአነሂ በኩርየ እሬስዮ
ወልዑል ውእቱ እምነገሥተ ምድር
ወለዓለም አዐቅብ ሎቱ ሣህልየ

እኔም ደግሞ በኩሬ አድርጌዋለሁ
ለዘለዓለም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ
ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው።

መዝ ፹፰፥፳፯

ምስጢር/ትርጉም፥ እኔም በኩረ ምዕመናን በኩረ ነገሥት አደርገዋለሁ በአራቱ ማዕዘን ከነገሡ ነገሥታት ይልቅ ልዑል ንጉሥ አደርገዋለሁ። (ልዑል ንጉሥ ነህ) ለእርሱም ለዘለዓለም ይቅርታዬን ምሕረቴን አጸናለሁ ማለት ነው።

ወንጌል፥ ማቴ ፪፥፩-፲፫
ቅዳሴ፥ እምቅድመ ዓለም (የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ)

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይሰርቅ ኮከብ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምስራኤል
(ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል የእስራኤልንም ኃጢአት ያስወግዳል)

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፲፩፥፳፭ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፬፥፩-፱ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፯፥፲፯-፳፫ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

## መድኃኒት ተወለደ (ተገለጠ)

የእግዚአብሔር የማዳን ቀን የመሲሁ መገለጫ ጊዜ ሲደርስ (ገላ ፬፥፬) ጨለማው በብርሃን የሚዋጥበት፤ ሟቹ ሕይወትን የሚለብስበት ቀን፤ የእግዚአብሔር እጅ ለማዳን የሚዘረጋበት ቀን፤ በሟች ባሕርይ ሕያው ባሕርይ የሚታይበት ጊዜ፤ የእግዚአብሔር ቀን ሲደርስ ቄሳር ዜጎቹን ለመቁጠር ፈልጎ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ሄደው እንዲቆጠሩ አዘዘ። የሰማይን ከዋክብት የሚቆጥረው፤ በየስማቸው የሚጠራቸው እናቱ የዳዊት ልጅ በመሆንዋ ለመቆጠር ወደ ቤተ ልሔም ወደ አባቷ ከተማ ሄደች። ነቢዩ ሚክያስ የተናገረውም ይፈጸም ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ያን ጊዜ ፀሐይ የሚወጣበት ሌሊት አልፎ መዓልት የሚወጣበት ወቅት ነበር። ሰማይና ምድርን የተሸከመችው ድንግል ከዮሴፍ ጋር ወደ ከብቶች በረት ሄደች። በዚያ ለመቆየት ከሸማግሌዎች ጻድቅ ጋር ወሰነች። እነዳዊት እነሰሎሞን ለክብር በተወለዱበት ቦታ አምላከ ዳዊት አምላከ ሰሎሞን የሚያርፍበት የክብር ቦታ ጠፋ። እመቤታችን የመውለጃዋ ወቅት ስለነበር በከብቶች በረት መሲሁን ወለደችው። በእርግጥም በዚያን ጊዜ ከነበሩ ሰዎች ጉባኤ የከብቶች በረት፤ ከሰዎቹም እንስሳቱ የተሻሉ ነበሩ። በመንግሥት ላይ ያሉት የንጉሠ ነገሥቱን መወለድ ሳይሰሙ መንጋ ጠባቂዎች ሰሙ። በጨለማ ያሉትን ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራ የመሲሁ መላእክትም በመሲሁ ብርሃን እየተደነቁ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እያሉ ዘመሩ። በጨለማ ላሉት እረኞች ታዩአቸው ለእረኞችም «መድኃኒት የሆነ ጌታ ክርስቶስም ተወልዶላችኋልና ደስ ይበላችሁ» ብለው የአእምሮ ጌታ በእንስሳት በረት፤ የዓለም ቅድስናም በቆሻሻ ሥፍራ መወለዱን ነገሯቸው። እረኞችም በቤተ ልሔም በበራው ብርሃን ተጉዘው መንጋዎቻቸውን ለሚጠብቅ አማናዊ እረኛ ትተው ወደ እግዚአ ኖሎት ጌታ ሄዱ። ሲሄዱም በጐል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅልሎ፤ የብርሃናት ጌታ ቅጠል ጨርቅ ለብሶ፤ የዘመናት ጌታ ህፃን ሆኖ ተወልዶ፤ የክብር ጌታ በደካማ ሥጋ ተገልጦ፤ ዘላለማዊነትን ያቋረጡት እግሮቹ የህፃናት እግሮች ሆነው፤ ሁሉን የሚይዘው የጌታ እጅ የእናቱን ጡት መያዝ በማይችል በህፃን ጣቶች ተውበው አዩ። የመላእክት ዝማሬ የቤተ ልሔሙ ዝማሬ ህፃን ክብር ብርሃን ሆኖ እረኞቹን ወደ ህፃኑ ሲመራ ኃጢአትን የሚያስወግደው የያዕቆብ ኮከብ ብርሃን ደግሞ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ሄደ፤ በጥበብ ሰዎች ልብ አበራ (ማቴ ፪፥፩-፲፫)። የሌሊቱን ማለፍ የመዓልቱን መምጣት አበሰረ (፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፱) እነሱም ወርቅ ለመንግሥቱ፤ ዕጣን ለክህነቱ፤ ከርቤ ለሞቱ እጅ መንሻ ይዘው ረጅሙን መንገድ በኮከቡ ብርሃን አቋረጡ። ወደ ኢየሩሳሌምም ሲደርሱ ኢየሩሳሌምና ንጉሥዋ ገና መድኃኒታቸውን አላወቁም ነበር። የቤተ ልሔምን ብርሃን አላዩም ነበርና በልባቸው ያደረው ሰይጣን የንጉሡን መወለድ ሲሰማ አስደነገጣቸው። የንጉሡን በዓት ባያውቁም ጠይቀው አመለከቱ። ሰብአ ሰገልም ቤተ ልሔም ደርሰው ንጉሡን በእናቱ እቅፍ በማየታቸው ተደሰቱ እጅ መንሻቸውንም ሰጡት።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን መድኃኒታችን የተገለጠው ለሚከተሉት ዓላማዎች ነበር።

አዳኙ ለምን ተገለጠ?

- የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ … (፩ኛ ዮሐ ፫፥፰)
- የጠፋውን ሊፈልግ፤ የተጎዳውን ሊፈውስ (ሉቃ ፲፱፥፲)
- ሕይወት እንዲበዛልን … (ዮሐ ፲፥፲)
- ዲያቢሎስን ከሥልጣኑ ሊሽር … (ዕብ ፪፥፲፬-፲፰)
- ኃጢአተኞችን ሊያድን … (፩ኛ ጢሞ ፩፥፲፭)
- ስለ እውነት ሊመሰክር … (ዮሐ ፲፰፥፴፯)
- በሕግ በነቢያት በመዝሙራት ስለራሱ የተጻፈውን ሊፈጽም … (ሉቃ ፳፬፥፵፬ ዮሐ ፭፥፵፮ ዮሐ ፲፱፥፴)
- ለድሆች ወንጌልን ሊሰብክ፤ ለታረዙት መፈታትን፤ ለእውሮች ማየትን፤ ለተጠቁት ነጻነትን፤ የጌታን ዓመት ሊሰብክ … (ሉቃ ፬፥፲፯-፳ ። ፵፫፥፵፬)
- የዘለዓለም ሕይወትን ሊሰጠን … (ዮሐ ፫፥፲፮)
- ጽድቅ ሊሆነን … (ሮሜ ፭፥፩-፪)

አዳኙ ምን ሆኖ ተገለጠ?

- ሰው ሆኖ … (ዕብ ፬፥፲፭)
- የሕይወት ረሃብ ላጠቃቸው የሕይወት እንጀራ ሆኖ … (ዮሐ፤ ፮፥፵፰-፶፱)
- በኃጢአት ጨለማ የሚመላለሱትን ከመሰናከል ሊያድናቸው «ብርሃን» ሆኖ … (ዮሐ ፰፥፲፪)
- እረኛ ላጡ በጎች ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ መልካም እረኛ ሆኖ … (ዮሐ ፲፥፲፩ ። ሕዝ ፴፬፥፩-፴)
- ሞት ላጠቃቸው፣ ሞት ተስፋ ላስቆረጣቸው ትንሣኤ ሕይወት ሆኖ … (ዮሐ ፲፩፥፳፭)
- ወደ እግዚአብሔር መድረስ ላልሆነላቸው (ላቃታቸው) መንገድ ለጠፋባቸው «መንገድ» ይሆን ዘንድ … (ዮሐ ፲፬፥፮)
- እውነትን በሐሰት ለሚለውጡ «እውነት» ጎስቋላ ሰው ነኝ ማን ያድነኛል ለሚሉ «ሕይወት» ሆኖ … (ሮሜ ፯፥፳፬-፳፭ ። ፩፥፲፰)
- የአንድነት የሦስትነት ምስጢር ላልተገለጸላቸው ከሣቴ ኅቡዓት ሆኖ … (ዮሐ ፲፬፥፴)
- በእርሱ የሚገባ ሁሉ ይድን ዘንድ በር ሆኖ (ዮሐ ፲፥፱)
- ጣፋጭ የወይን ግንድ ሆኖ … (ዮሐ ፲፭፥፩)

በሐዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረን ዘንድ ፍጡር ሥጋን ለበሰ፤ በአምሳያው ሁለተኛ ይወልደን ዘንድ በአምሳያችን ተወለደ። ክብር ለእርሱ ይሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM